የገቢዎች ሚኒስቴር
Ministry of Revenues

# ሞጁል አራት

# የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሠልጠኛ ሞጁል

የታክስ ጉዳዮች ትምህርት ዳይሬክቶሬት



ሐምሌ/2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

መግቢያ……………………………………………………………………………3

ክፍል አንድ አጠቃላይ ሁኔታ…………………………………………………………4

1.1. ዓላማ……………………………………………………………………………4
1.2. ውጤት…………………………………………………………………………4
1.3. ወሰን……………………………………………………………………………5
1.4. ትርጓሜ…………………………………………………………………………5

ክፍል ሁለት…………………………………………………………………………7

2.1 የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንነት ……………………………………………7

2.2 የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ትርጉም…………………………………………………7

2.3 የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቀሜታዎች……………………………………………8
2.4 ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች (Taxable supplies)………………………8
2.5 የታክሱ ከፋዮች…………………………………………………………………9
2.6 ከተጨማሪ ዕሴት ታስ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች……………………………………10
2.7 የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎች /Rates…………………………………14
2.7.1 አስራአምስት በመቶ መጣኔ (መደበኛ መጣኔ)……………………………14
2.7.2 በዜሮ መጣኔ /0%/ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች……………………14
ክፍል ሦስት…………………………………………………………………………16
3.1 ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ስለመመዝገብ……………………………16

3.1.1 የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች የምዝገባ ጊዜና ሥርዓት……………………16
3.2 ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የሚከናወኑበት ቦታ፣ጊዜና እሴት /ዋጋ…………17

3.2.1 የዕቃዎች አቅርቦት የሚከናወንበት ቦታ………………………………………17

3.2.2 አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ……………………………………………………18

3.3 አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ…………………………………………18
3.4 ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እሴት /ዋጋ/…………………………………19

ክፍል አራት..........................................................................................21

4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማቀናነስ እና ተመላሽ.......................................21

4.1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ..................................................19

4.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመላሽ ስርዓት............................................25

4.2.1 የታክስ ተመላሽ የሚፈቀድባቸው ግብይቶች........................................26

4.2.2 መደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስርዓት አፈፃፀም........................29

4.2.3 ከተ.እ.ታ ነፃ በተደረገ ሰው ላይ የሚፈፀም የታክስ ተመላሽ ሥርዓት............29

4.2.4 የታክስ ተመላሽ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ........30

4.2.5 የልዩ ባለመብቶች የሚከፍሉት አገልግሎት ክፍያ ከታክሱ ነፃ ስለመደረጉ.......34

4.2.6 በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ...................................35

4.2.7 የወኪሉ ግዴታ..........................................................................36

ክፍል አምስት..........................................................................................38

5. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ማሳወቅ፣ስረዛ ፣አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች.......38

5.1. ማሳወቅ....................................................................................38

5.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ስረዛ ጊዜና ሥርዓት..............................38

5.3. በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ስረዛ ጊዜ ስለሚታሰብና ስለሚቀናነስ ታክስ...39

ክፍል ስድስት..........................................................................................40

6. ከተጨማሪ ዕሴት ጋር የተያያዙ አስተዳራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች...................40

6.1. አስተዳደራዊ ቅጣቶች....................................................................40

6.2. የወንጀል ቅጣቶች........................................................................41

ማጠቃለያ..............................................................................................43

ማጣቀሻ................................................................................................44

## መግቢያ

የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀጥተኛ ካልሆኑ የታክስ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ታክሱ በእቃዎችና በአገልግሎቶች አቅርቦት ላይ የሚጣል "የፍጆታ ታክስ" ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህ ታክስ በፍጆታ ላይ ወይም በተጠቃሚው ወጪ ላይ የተመሠረተ ታክስ ነው፡፡ ታክሱ በተጠቃሚዎችላይ የተመሰረተ ሲሆን የሚሰበሰበው ምርት ከውጪ ወደ አገር ሲገባ / ማንኛውንም ታክሱ የሚከፈልበት የዕቃ /የአገልግሎት ግብይት ሲካሄድ ነው፡፡ ተጨማሪ እሴት ታክስ ከአስመጪዎችና ከጥሬ ዕቃ አምራቶች አንስቶ እስከ ችርቻሮ ድረስ በሚደረጉ የማምረትና የማከፋፈል ሂደቶች ተጨማሪ እሴት ታክስ ይሰበሰባል፡፡

በዚህ ሞጅል ግልፅ የሆነ የታክስ ትምህርት በመስጠት ታክስ ከፋዮች ስለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ፣ ስረዛ፣ ማቀናነስ፣ ስለተመላሽ፣ በገኘው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች ላይ በቂ እውቀት እንዲኖር ለማድረግ በሰባት ክፍል የተከፋፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስተማሪያ ሞጁል ነው፡፡

# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ ሁኔታ

## 1.1. ዓላማ

### ❖ ዋና ዓላማ

ከሥልጠናው በኋላ ሠልጣኞች፤

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት የሥልጠና ሞጁሉን በመገንዘብ እና ውይይት በማድረግ ስለተጨማሪ እሴት ታክስ ይረዳሉ፡፡

### ❖ ዝርዝር ዓላማ

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንነት እና ከታክሱ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶችን ይለያሉ
- የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎች ያብራራሉ፤
- በዜሮ መጣኔ እና ከታሱ ነጻ በሆኑ አቀርርቦቶች መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራሉ
- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የምዝገባ ስርዓት ይልጻሉ
- ታክሱ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ስለሚከናወኑበት ቦታ፣ ጊዜና ዋጋ ያብራራሉ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ በምሳሌ ያስረዳሉ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ የሕግ አግባቡን በማስረዳት ተመላሽ የሚፈቀድባቸውን ግብይቶች ይለያሉ፤
- ከተጨማ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ለመሰረዝ የሚያበቁ መስፈርቶችን ይዘረዝራሉ
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች ይለያሉ፡፡

## 1.2. ውጤት

- ታክስ ከፋዮች ስለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ፣ ስረዛ፣ ማቀናነስ፣ ስለተመላሽ፣ በገኘው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች ላይ በቂ እውቀት ያገኛሉ፡፡
- ሕግ እና ሥርዓቱን መሠረት በማድረግ ወቅቱን ጠብቀው የተጨማሪ እሴት ታክስን አሳውቀው ይከፍላሉ፡፡

## 1.3. ወሰን

- **የሰነዱ ሽፋን**

የሰነዱ ሽፋን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 609/2001፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 1157/2011፤ የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማስከፈል በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ቁጥር 79/1995፤ ስለፌደራል የታክስ አስተዳደር የወጣ ደንብ ቁጥር 407/2009፤ ለተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/1996፣ 21/1997፣ 24/2001፣ 148/2011 እና በገኘው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2012 እንዲሁም የገንዘብ ሚኒስቴር ሰርኩላር ቁጥር ታ/ከ/ቀ/5/161 ቀን 26/03/2010 ዓ.ም ናቸው።

- **የሥልጠና ተሳታፊዎች**

ሥልጠናው፤ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች የሚሰጥ ሲሆን የድርጅቱ/ፒኤልሲው ሥራ አስኪያጅ፣ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እና የፋይናንስ ክፍል ሠራተኞች፤የዕሽሙር ማህር፤ ወይም ሌላ የሚመለከተው ባለሙያ (ማርኬቲግ ማናጀሩ/የሽያጭ ሠራተኛ) እንዲሁም የታክስ እንደራሴዎች ይሠለጥናሉ።

- **ጊዜ**

ሥልጠናው የሚሰጠው ለ16 ሰዓታት ነው።

## 1.4. ትርጓሜ

- **የግብዓት ታክስ** ፡-አንድን ምርት ለማረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት በሚፈጸም ግዢ ላይ የሚከፈል የተጨማ ዕሴት ታክስ ነው።
- **የምርት ውጤት ታክስ፡-** ምርት በሚሸጥበት /አገልግሎት በሚሰጥበት/ወቅት በመሸጫ ዋጋው ላይ ታስቦ የሚከፈል የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነው።
- **ተከፋይ ተጨማ ዕሴት ታክስ፡-** ግብር መክፈል ባለበት ሰው ለፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባስልጣን በታክስ አዋጁ መሰረት የሚከፈል የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነው።
- **ዜሮ መጣኔ፡-** አቅርቦቱ ዜሮ ከመቶ የሚከፈልበት ሆኖ ነገር ግን ለአቅርቦቱ በግዥ ወቅት የተከፈለ የተጨማ ዕሴት ታክስ ተመላሽ/ማካካሻ ሊጠየቅበት ይችላል።

ሌሎች ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላትና ሀረጎች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 609/2001፤ የተጨማሪ እሴት

ታክስ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 1157/2011፤ የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማስከፈል በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ቁጥር 79/1995፤ ስለፌደራል የታክስ አስተዳደር የወጣ ደንብ ቁጥር 407/2009፤ ለተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/1996፣ 21/1997፣ 24/2001፣ 148/2001 እና በገኘርው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2012 የተሰጠ ትርጉም ይይዛሉ።

## ክፍል ሁለት

### 2.1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንነት

- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከሌለሎች የታክስ አይነቶች አንጻር ሲታይ የቅርብ ጊዜ ታክስ ሲሆን እንደ ጎርጎሮሲያን አቆጣጠር በ20ኛው ክፍለዘመን የመጀመሪያዎቹ አካባቢ (ከ1960 -1970ዎቹ) ባሉት ጊዚያት ውስጥ እንደተጀመረ ይነገራል፡፡
  - የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የራሱ የሆነ መጣኔ ያለው ሲሆን እንደየሀገሮቹ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካ እና የዕድገት ደረጃ የተለያየ ነው፡፡
  - Accounting & Finance blog በ2016 ባሰፈረው ጽሑፍ በዓለም ላይ ከፍተኛ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መጣኔ ያላቸው ሀገራት

1. የደቡብ ኢሲያዋ ሀገር ቡህታን (50%)፣
2. ጅቡቲ (33%)
3. ቡርማ /ማይናማር (30%)
4. ሃንጋሪ,ኖርዌ ,ስዊድን እና ደንማርክ (25%)

- Woltres kluwer (በ2017 ባሰፈረው ጽሁፉ ከአውሮፓ እና ከኢሲያ ሀገራት ዝቅተኛ የተጨመሪ ዕሴት ታክስ መጣኔ ያለቸው ሀገራት ህንድ ከ12-15%፤ጃፓን 5% ሲወዘርላንድ ከ8-2.5%፤መጣኔ ያላቸው ሲሆን አብዛኞቹ ሀገራት በወጪ ንግድ ላይ 0% መጣነኔ እንዳላቸው ያሳያል በኛም ሀገር ሁለት መጣኔዎች ያሉ ሲሆን 15 እና 0% መጣኔ ናቸው፡፡

### 2.2. የተጨማሪ ዕሴት ትርጉም

- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መሰረቱ ሰፊ የሆነ በፍጆታ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የሚጣል ቀጥታ ያልሆነ ታክስ ነው፡፡ ታክሱ ከአስመጪዎችና ጥሬ ዕቃ አምራቾች አንስቶ እስከ ቸርቻሮዎች ድረስ በሚደረጉ የማምረትና የማከፋፈል/የማሰራጨት/ሂደቶች በሁሉም ደረጃዎች በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት ላይ ይሰበሰባል፡፡
  - የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚመረቱና ከውጭ አገር በሚገቡ ዕቃዎችና ሌሎችም አገልግሎቶች ላይ የሚሰበሰበውን የሽያጭ ታክስ ተክቶ ከታህሳስ 23 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለ ታክስ ነው፡፡
- የሽያጭ ታክስ በጥሬ ዕቃ ላይ የተከፈለን ታክስ ብቻ ተመላሽ የሚያደርግ ሲሆን፤ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ግን ለማምረቻ መሳሪያዎች፤ለማፋፈል እና ለአስተዳደራዊ ተግባራት የተከፈለን ታክስ ጭምር ተመላሽ ያደርጋል፡፡

### 2.3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቀሜታዎች

- ➢ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ከውጭ ከሚገቡ ምርቶች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይረዳል፣
- ➢ ለካፒታል ዕቃዎች የሚደረገው የታክስ ተመላሽ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፡፡
- ➢ ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ
  - ✓ ለግብዓቶች የተከፈለው ታክስም ተመላሽ የሚደረግ በመሆኑ
- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም በደረሰኝ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን በመሆኑ
  - ✓ በቀላሉ ሳይከፈል ሊታለፍ ወይም
  - ✓ ሊጭበረበር የሚችል ታክስ ባለመሆኑ
  - ✓ የታክስ ስወራንና ማጭበርበርን በመቀነስ
  - ✓ በታክስ ሕግ አፈፃፀም ሊኖር የሚገባን ትክክለኛነትና ፍትሐዊነት በተሻለ አኳኋን ያስጠብቃል፡፡
- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት አነስተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሚዛናዊ ያልሆነ ጫና እንዳይፈጠር ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ እቃዎችና አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## 2.4. ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች (Taxable supplies)

- ➢ ታክሱ የሚጣለው በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ማናቸውም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ነው፡፡
- ➢ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማለት ደግሞ
  - ✓ በህጉ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር፤
  - ✓ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት
  - ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀርብ ወይም ወደ ሃገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው፡፡
- ❑ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ" ማለት ፤-
  - ➢ ለትርፍ የተከናወነ ቢሆንም ባይሆንም ጥቅም ለማግኘት ሲባል ለሌላ ሰው በሙሉ ወይም በከፊል ዕቃ የመሸጥ ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባርን ለማከናወን በማሰብ ወይም በትክክል በማከናወን ማንኛውም የተመዘገበ ሰው በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ ነው፡፡(amended)
- ➢ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ተደርገው የሚቆጠሩ

- የተመዘገበ ሰው ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የገዛቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ ያደረገ እንደሆ፤
- አሠሪው ለሠራተኞቹ በስጦታ ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣
- ምዝገባ ሲሰረዝ የካፒታል ዕቃዎችን ጨምሮ በተመዘገበው ሰው እጅ የሚገኙ ዕቃዎች፣
- ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አንድ ክፍል ሆኖ ተለይቶ በራሱ የሚንቀሳቀስ ክፍል የተሸጠ እንደሆነ፣

❑ **ቅጥይ አቅርቦቶች**

- የዋና አቅርቦት ወይም አገልግሎት የመስጠት ንግድ ሥራ ተጓዳኝ የሆኑ የዕቃና የአገልግሎት አቅርቦቶች የዋናው ዕቃ አቅርቦትና አገልግሎት የመስጠት ሥራ አንድ ክፍል ሆነው ይቆጠራሉ፣ምሳሌ ጋራዥ አገልግሎት ዋናው ስራ ሆኖ የጋራዡን ስራ ለማሳለጥ የሚጠቀምባቸው ዘይት የጋራዡ አንድ ክፍል ሆነው ይቆጠራሉ
- ዕቃን ወደ አገር ከማስገባት ሥራ ጋር ተጓዳኝ ሆነው የተሰጡ አገልግሎቶች ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች አካል ይሆናሉ፤ ለምሳሌ አሳንስሩን ከውጭ አስመጥቶ ባሃገር ውስጥ ለማስገጠም ቢሞክር አሳንሰሩን የሚገጥሙ ባለሞያዎች አብረው ቢመጡ የዋናው አገልግሎት አንድ ክፍል ሆነው ይቆጠራሉ
- ከታክስ ነፃ የሆነ አንድ ግብይት ታክስ የሚከፈልባቸው የተለያዩ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የማቅረብ ሥራዎች ያካተተ ሲሆን የተለያዩ ግብይቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፣ ለምሳሌ (phermacy)፡፡

## 2.5. የታክሱ ከፋዮች

- የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበት ሰው፣
- ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባ
- ወደ አገር የሚገቡ አገልግሎቶችን በሚመለከት (በገኘው ስለሚሰበሰብ ታክስ) መሠረት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው፣
- ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ምዝገባው ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ ታክስ ከፋይ ነው፡፡
- መመዝገብ ያለበት ሆኖ ያልተመዘገበ ሰው ደግሞ የምዝገባ ግዴታ ከሚጀምርበት ጊዜ ቀጥሎ ያለው የሂሳብ ጊዜ ከሚጀምርበት አንስቶ ታክስ ከፋይ ነው፡፡

## 2.6. ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች

- ከታክሱ ነጻ የሆኑ ዕቃዎች እና አገልግቶች ማለት ምንም አይት የተጨማ ዕሴት ታክስ /በመደበኛም ሆነ በዜሮ መጣኔ/የማይከፈልባቸው አቅርቦቶች ማለት ነው፡፡
- በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባም በአጠቃላይ አመታዊ ሽያጭ ውስጥ አይታሰቡም
- አንድ ግብር ከፋይ ሙሉ በሙሉ ከታክስ ነጻ በሆኑ ግብይቶች ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ግብር ከፋይነት አይመዘገብም፡፡
- አንድ ግብር ከፋይ ቀይጥ አቅርቦት የሚያከናውን ቢሆን ማለትም ታክስ የሚከፈልበት እና ከታክስ ነጻ አቅርቦቾች ላይ የተሰማራ ቢሆን ከታክስ ነጻ ለሆኑት አቅርቶቹ የግብዓት ታክስ ማካካሻ መጠይቅ አይችልም፡፡

### ❑ የሚከተሉት ከታክሱ ነጻ የተደረጉት አቀርቦቶች ናቸው

ሀ)‹‹ በንግድ መልክ ለማረፊያነት የሚከራዩ ክፍሎች›› ማለትም ፡-

I. በሆቴል፣በሞቴል፣በገጠር ማረፊያ፣ በማደሪያ ቤት፣በሆስቴል ወይም በተመሳሳይ ተቋም ለአምስት እና ከአምስት በላይ ለሆኑ ሰዎች በየቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ ወይም በሌላ የተወሰነ ጊዜ ክፍያ በመጠየቅ የሚሰጥ የማረፊያ አገልገሎት፤

II. በተራ ቁጥር I እና III በተመለከተው ትርጉም የማይሸፈን ለእያንዳንዱ ተከራይ በተከታታይ ከ35 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የሚከራይ ማናቸውም ቤት፣ በፎቅ ውስጥ ያለ መኖሪያ አፓርትመንት ወይም ክፍል ሲሆን ዓመታዊ የኪራይ ገቢው ከብር 24 ሺ የሚበልጥ ወይም ይበልጣል ብሎ ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለ፤

III. የንግድ ሥራ ድርጅት የተከራየውን ንብረት ወይም ተለይቶ የሚታወቅ የአንድ የንግድ ስራ ድርጅት ንብረት ጨምሮ ለመኖሪያ የሚያገለግል ማናቸውም ቤት በፎቅ ውስጥ ያለ መኖሪያ አፓርትመንት ክፍል ተንቀሳቃሽ ቤት የጀልባ ቤት ድንኳን የመስክ ስፍራ የሚያስተዳድር ሰው፤

- የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን በማከናወን ሂደት አምስት እና ከአምስት በላይ የሆኑ ቤቶችን በፎቅ ውስጥ ያሉ ክፍሎችን አፓርትመንቶችን ክፍሎች ተንቀሳቃሽ ቤቶችን የጀልባ ቤቶችን ወይም ተንቀሳቃሽ ለመዝናኛ የተዘጋጁ ስፍራዎችን የሚያከራይ ወይም ለኪራይ የያዘ፤

- ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ለመዝናኛ በማከራየት የሚያገኘው ዓመታዊ የኪራይ ገቢ ከብር 24 ሺ በላይ ከሆነ ወይም ይህ ዓመታዊ ገቢ ከተጠቀሰው ገንዘብ መጠን ይበልጣል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ካለ፤
- በመደበኛ ሁኔታ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የሚያከራይ ወይም ለማከራየት የያዘ ከሆነ ወይም

IV. ሌላ ማናቸውም ለመኖሪያ የሚውል እና የገቢዎች ሚኒስትር በንግድ መልክ ለማረፊያነት የተቋቋመ ነው በሚል የሚመድበው ድርጅት ነው፡፡ ሆኖም በአንቀጽ v vI እና vII የተገለጸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አይጨምርም፡፡

V. ለቀጣሪው ወይም ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ጥቅም ለማስገኘት ሳይሆን ድርጅቱ ወይም ሆስቴሉ ለቀጣሪው ወይም ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ጥቅም የሚያውለው ማናቸውም ማደሪያ ተቋም ወይም ሆስቴል፤

VI. በየአካባቢ ባለስልጣኖች የሚተዳደሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የማረፊያ ተቋሞች ወይም ሆስቴሎች፤

VII. በማናቸውም የተመዘገበ ሆስፒታል የማዋለጃ ድርጅት ወይም ክሊኒክ የሚሰጥ አገልግሎት፡፡

ለ) ‹‹መኖሪያ ቤት›› ማለት ማናቸውም በዋነኛነት ለመኖሪያ የሚያገለግል ወይም ለመኖሪያነት እንዲውል የታቀደ ሕንፃ ወይም ሌላ ማናቸውም ቦታ እና የእነዚሁ ተቀፅላዎች ሲሆን በንግድ መልክ ለማረፊያነት የሚከራዩ ክፍሎችን አይጨምርም፡፡

i. ወደ ወጪ ከሚላኩት ዕቃዎች በስተቀር ዓይነታቸው ቀጥሎ የተመለከቱት የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች አቅርቦት እንዲሁም ገቢ ዕቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ነፃ ናቸው፣

- ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፤
- የፋይናንስ አገልግሎቶች፣
- የአገር ውስጥና የውጭ አገር ገንዘቦችን እና የዋስትና ሰነዶችን ማስራጨት ወይም ወደ አገር ማስገባት፣(ለሣንቲሞች እና ሜዳሊያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚውሉት በስተቀር)
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ማስገባት፣
- በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣(ይህ ማትለት ግን ለግንባታ አገልግሎት ግብዓት ሲገዙ፤ የቢሮመገልገያዎችን ሲገዙ…ከታሱ ነጻ አይደሉም
- የሕክምና አገልግሎት እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት

- ✓ በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች፣
- ✓ የህክምና አቅርቦቶች እና የህክምና መገልገያዎች፣

- ➢ በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች(ተማሪው የሚከፍለው የትህርት ክፍያ ላይ ቫት አይሰበሰብም ማለት ሲሆን ነገርግን ተቋሙ ህንጻ ሲያስገተነባ፤ ሲከራይ እና ጠረንጴዛና ወንበሮችን ሲያስገጥም የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡
- ➢ ለሕፃናት ጥበቃ በመዋለ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣
- ➢ በሰብዓዊ እርዳታ መልክ የሚቀርቡ ዕቃዎች እና የሚሰጡ አገልግሎቶች
    - ✓ እንደዚሁም በተፈጥሮ አደጋ፣
    - ✓ የኢንዲስትሪ አደጋዎችና በድንገት ለደረሱ ጉዳቶች መልሶ ማቋቋሚያ ተግባር እንዲውሉ ለመንግስት አካላት እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጡ ከውጪ አገር የሚገቡ ዕቃዎች፣
- ➢ የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲንና የውሃ አገልግሎቶች፣(የታሸገ ውሃ አይጨምርም)
- ➢ በሕግ ወይም በስምምነት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ከሌሎች ታክሶች ነፃ የተደረጉ ድርጅቶች፣ ተቋሞችና ፕሮጀክቶች ወደ አገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣
- ➢ ከልዩ ልዩ የአገልግሎት ወይም የኮሚሽን ክፍያዎች በስተቀር የፖስታ አገልግሎት ድርጅት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፤
- ➢ የትራንስፖርት አገልግሎት፤ (ለትራንስፖርት አገልግሎት የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት በማናቸውም ዓይነት ትራንስፖርት ሰዎችን ወይም ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የሚፈፀምን ክፍያ ያካትታል፡፡)
- ➢ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግስት የሚፈፀም ክፍያ፣(አላማቸው ለህብረተሰቡ አገልግሎት ለመስጠት ስለሆነ)
- ➢ በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ 2ኛ መደብ የተዘረዘሩ ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባት፣ (ለፋብሪካ የሚቀርብ ጥሬ ዕቃ፣ታሪፋቸው ዜሮ የሆኑ፡-ካፒታል ዕቃዎች. . .
- ➢ ከስድሣ በመቶ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣(አካል ጉዳተኞችን ከማበረታታት አንጻር የታየ ነው እንዲሁም ኢንቨስተሮች አካል ጉዳተኞችን ትኩረት ያደረገ ኢንቨስተርን ለማብዛትም ጭምር ታስቦ ነው
- ➢ የምግብ እህሎች /ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጥራጥሬ እና የመሣሠሉት፣

- በግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ኪራይ አገልግሎት የሚከናወኑት (ከጥቅምት 23/2012 ዓ.ም. ጀምሮ ገ/ሚ/ር በቁጥርME-30/58/9)
    - ✓ የማሳ ዝግጅት፣ምንጣሮ፣መሬት መደልደል፣
    - ✓ የመስኖ ቦይ ማወጣትና ማዘጋጀት፣
    - ✓ አጨዳ፣ውቂያ፣ዘር መዝራት፣ኬሚካል መርጨት፣
    - ✓ ምርት ማበጠር፣ ገለባ መሰብሰብና ማሰር፣ወሃ ፓምፕ፣
    - ✓ የመኖ ማቀነባበር እና ምርት ከማሳ ወደ ጎተራ ማጋጋዝ..
- ለወባ መከላከያ አጐበር ስራ የሚውሉ
    - ✓ የስፌት ክር ሌብል፣ ማሸጊያ ፕላስቲክ እና ማዳበሪያ፣
    - ✓ አጐበሩን ለመስፋት የሚያገለግል በኬሚካል የተከገረ ጨርቅ
- የቆዳ ፋብሪካዎች የሚያደርጉት የፒክል፣ የዌት ብሉ እና የክረስት ምርት ግብይት፣
- የቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ፋብሪካዎች ለጫማ ፋብሪካዎች የሚሸጡት የተጠናቀቀ ቆዳ፤
- ከፖልም የተሰራ የምግብ ዘይት፣የእንጀራ፣ ዳቦ እና የወተት ሽያጭ፣የወተት ተዋጽኦን ግን አያካትትም
- ለግብርና ምርት የሚውሉ ማዳበሪያዎች፣ ምርጥ ዘር፣ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች፣
- የጡረታ አበል ክፍያ አገለግሎት፣
- የጉዞ ወኪሎች የአውሮፕላን ቲኬት በመሸጥ የሚሰጡት የገበያ አገልግሎት፣
- የቡታጋዝ ምርት፣
- በሕግ ወይም በስምምነት ከታክሱ ነፃ የተደረጉ ወደ አገር የሚገቡ

❑ **በስምምነት ከታክሱ ነፃ የተረጉ የሚለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይጨምራል፡፡**

- በኢትዮጵያ መንግስትና በማናቸውም ድርጅት ወይም በማናቸውም አገር መንግስት መካከል የተደረገ የቴክኒክ ትብብር ወይም የሰብዓዊ ዕርዳታ ስምምነት
- በዲፕሎማቲክ ልዩ መብቶችና ጥቅሞች ደንብ የተፈቀደ
- የኢትዮጵያ ሕግ አካል በሆነ ዓለም አቀፍ ስምምነት
- ማናቸውም ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ሌላ የባለ ብዙ ወገን ስምምነት

## 2.7. የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎች /Rates

❑ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ሁለት የታክስ መጣኔዎች ይኖሩታል፡፡ እነሱም 15 ከመቶ መደበኛ መጣኔና ዜሮ ከመቶ መጣኔ የሚባሉት ናቸው፡፡

### 2.7.1. አስራአምስት በመቶ መጣኔ (መደበኛ መጣኔ)

- ❑ በተመዘገቡ ሰዎች የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት፡-
- ✓ "ታክስ የሚከፈልበት ግብይት" ማለት ከታክስ ነፃ ከተደረገው አቅርቦት በስተቀር ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የሚከናወን ማናቸውም የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች አቅርቦት ነው፡፡
- ✓ በተመዘገበ ሰው ስለሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተቀመጠው መመዘኛ ባልተመዘገቡ ሰዎች የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንደማይመለከተው ያመለክታል፡
- ✓ ሆኖም የተመዘገበ ሰው የንግድ ስራ ዕቃዎቹን ለግል ጥቅም ያዋላቸው ከሆነ የነዚህ ዕቃዎች አቅርቦት ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ እንዳዋላቸው ይቆጠራል፡፡
  - ➢ ከታክስ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር በማናቸውም ወደ አገር የሚገቡ
- ✓ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች

## 2.7.2. በዜሮ መጣኔ /0%/ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች

- ➢ ለውጭ የገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (Exports)
- ➢ ዓለም አቀፍ የዕቃ ወይም የመንገደኞች የማጓጓዝ ተግባር፣ እንዲሁም በጉዞው አገልግሎት ላይ የሚውሉ የፍጆታ አቅርቦቶች፤ዓለም አቀፍ ጉዞው በአየር፣በባቡር፣ በመርከብ፣በየብስ የሚደረጉ ጉዞዎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡(እንደቅባት፣ዘይቶች እና ሌሎች አላቂ የቴክኒክ እቃዎች በቀጥታ ከጉዞው ጋር የተገናኙ መሆን አለባቸው
- ➢ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፣
- ➢ አንድ የተመዘገበ ሰው ለሌላ የተመዘገበ ሰው አንድ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ራሱን ችሎ የሚሰራ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ክፍል /ሀብት/ ላልተወሰነ ጊዜ ይንቀሳቀሳል ተብሎ ለተቋቋመ ድርጅት ሲያስተላለፍ
- ➢ ዜሮ ከመቶ መጣኔ /0%/ ታክስ ይከፈልባቸዋል ሲባል ከእነዚህ ግብይቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ አይሰበሰብም ማለት ነው፡፡
- ➢ አቅርቦቶቹ የሚቆጠሩት ታክስ እንደሚከፈልባቸው አቅርቦቶች (Taxable Suppiles) ሲሆን፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በአጠቃላይ ዓመታዊ ሽያጭ ውስጥ ይታሰባሉ፡፡

  እነዚህን አቅርቦቶች የሚያመርትና አገልግሎት የሚሰጥ ሰው በግብዓት ላይ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ/ተመላሽ ለማግኘት ይችላል፡፡

### የሙከራ ጥያቄዎች

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንነት እና ከታክሱ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶችን ይለዩ
- የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎችን አብራሩ
- በዜሮ መጣኔ እና ከታሱ ነጻ በሆኑ አቀርርቦቶች መካከል ያለውን ልዩነት ያርራሉ

# ክፍል ሦስት

## ❑ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ እና ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የሚከናወኑበት ቦታ፣ጊዜ እና ዕሴት

### 3.1. ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ስለመመዝገብ

- አንድ ግብር ከፋይ በማናቸውም ሁኔታ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከ1ሚሊዮን ብር በላይ ከሆነ እና
- በቀጣዮቹ 12 ወራት የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከ1 ሚሊን ብር በላይ ይሆናል ተብሎ ለመገመት ተጨባጭ ማስረጃ ከተገኘ ታክስ ከፋዩ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ በግዴታ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡
- ግብር ከፋዮች በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወኑት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት 1ሚሊየን ብር እና ከዛ በታች ከሆነ፤ በማናቸውም ተከታታይ 12 ወራት ጊዜ ውስጥ ሽያጩን ቢያንስ 75% ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ሰዎች የሚያቀርብ ከሆነ ዓመታዊ ሽያጩ ብር 1ሚሊን ባይሞላም በፈቃደኝነት መመዝገብ ይችላል፡፡ ምዝገባ የሚወሰነው በታክስ ባለሥልጣኑ ሲሆን፤ ቀጥሎ የተመለከቱትን እንዳይመዘገቡ ሊቃወም ይችላል፤
    - ቋሚ የመኖሪያ /ማሪፊያ/ ቦታ ወይም የንግድ ሥራ አድራሻ የሌለውን፣
    - ተገቢ የሂሳብ መዛግብት የማይዘውን፣
    - የባንክ ሂሳብ የሌለውን እና
    - ቀደም ሲል ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሆኖ ነገር ግን በታክስ ህጉ መሠረት ግዴትዎቹን ለመፈፀም ያዳገተው እንደሆነ፡፡

#### 3.1.1.የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች የምዝገባ ጊዜና ሥርዓት

ማንኛውም ሰው/ድርጅት ታክሱ የሚጣልበትን ግብይት የሚያከናውን ሆኖ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ የተዘረዘሩ ሁኔታዎችን አሟልቶ የገቢዎች ሚኒስትር ባዘጋጀው ቅፅ ማመልከቻውን ሲያቀርብ ባለስልጣኑ አመልካቹን በተጨማሪ እሴት ታክስ ይመዘግበዋል፡፡ ከመዘገበ በኂላ ከምዝገባው ዕለት ጀምሮ ባሉት በ 30 /ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ፡-

1. የተመዘገበውን ሰው ሙሉ ስምና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች
2. የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበትን ቀን
3. ተፈፃሚነቱ የሚጀምርበትን ቀን

4. የተመዘገበው ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሚሉ መረጃዎችን የያዘ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

የምዝገባ ጊዜውን በተመለከተ **የግዴታ ምዝገባ** ሲሆን ለምዝገባ የማመልከቻ ማቅረብ ግዴታ ከሚጀምርበት ወር ቀጥሎ ባለው የሂሳብ ጊዜ የመጀመሪያ ቀን እንዲሁም **ምዝገባ በፍቃደኝነት** ሲሆን ደግሞ አመልካቹ ለምዝገባ ማመልከቻ ካቀረበበት ወር ቀጥሎ ባለው የሂሳብ ጊዜ የመጀመሪያ ቀን መሆን አለበት፡፡

በፈቃደኝነት ለመመዝገብ የሚያመለክት ሰው የተወሰነ የመኖሪያ ወይም የንግድ ሥራ አድራሻ የሌለው፣የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ፣ጊዜውን ጠብቆና በአስተማማኝ ሁኔታ ታክስ የማያስታውቅ ስለመሆኑ ባለስልጣኑ አሳማኝ ምክንያት ካለው ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ምዝገባው ተጠናቆ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከመሆናቸው በፊት እስከቆዩበት የመጨረሻ ቀን ድረስ ባካሄዱት ግብይት ላይ የተርን ኦቨር ታክስ ይከፈልበታል፡፡

## ❑ ታክስ የሚከፈልበት የግብይት ዋጋን ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውል መረጃ

ለታክሱ ለመመዝገብ የተቀመጠውን አመታዊ የግብይት ዋጋ ለማወቅ ወይም ለመገመት የሚያስችል ታክስ የሚከፈልበት የግብይት ዋጋን ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎች:-

I. ግብር ከፋዮቹ በታክስ ማስታወቂያ ወቅት የገለፁት የገቢ መረጃ፣
II. ከሦስተኛ ወገን የተገኘ መረጃ ወይም
III. በሂሳብ ምርመራ ወቅት የተገኘ መረጃ፡፡

## 3.2. ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የሚከናወኑበት ቦታ፣ጊዜና እሴት /ዋጋ

### 3.2.1.የዕቃዎች አቅርቦት የሚከናወንበት ቦታ

- አቅርቦቱ ዕቃዎችን ማጓጓዝን የሚጨምር ሲሆን ሽያጩ ተከናወነ የሚባለው ዕቃዎችን ማጓጓዝ የሚጀምርበት ቦታ ይሆናል፡፡
- በሌሎች ሁኔታዎች የተሸጠው ዕቃ ርክክብ የሚፈፀምበት ቦታ ነው፡፡
- የኤሌክትሪክ፣ የእንፋሎት ኃይል፣ የጋዝ ወይም የውሃ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ፣ አገልግሎቱ ተሰጠ የሚባለው አገልግሎቶቹ ተቀባዩ ዘንድ በደረሱ ጊዜ ነው፡፡

- እነዚህ አቅርቦቶች ከኢትዮጵያ ውጪ የሚላኩ ከሆነ ግን አቅርቦቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡

## 3.2.2. አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ

- ❑ አገልግሎት የሚሰጠው ሰው የንግድ ስራ ተግባሩን የሚያከናውንበት ቦታ ነው፡፡
- ❑ ከዚህ በተለየ ሁኔታ የሚታዩት የአገልግሎት አይነቶች የሚሰጡበት ቦታ የሚባለው፡-
  - ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ የተገናኘ ከሆነ ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ፣
  - ከሚንቀሳቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ የተገናኘ ሲሆን፣ አገልግሎት መስጠቱ የተከናወነበት ቦታ፣
  - በባህል፣ በስነጥበብ፣ በትምህርት፣ የሰውነት ማጐልመሻ ወይም በስፖርት ወይም በሌሎች መሰል ዘርፎች ሲሆን አገልግሎቱ የተሰጠበት ቦታ
  - ከማጓጓዝ ተግባር ጋር የተያያዘ ከሆነ የማጓጓዝ ተግባሩ የተከናወነበት ቦታ ነው፡፡
  - በዜሮ መጣኔ ታክስ የሚከፈለበትን አለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት በተመለከተ የግብይቱ ተግባር ታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ ውጭ ከሰጠው አገልግሎት ጋር የተገናኘ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡
- ❑ የሚከተሉት አገልግሎቶች የሚሰጡበት ቦታ አገልግሎቱን የገዛው ሰው ዘላቂ ድርጅት የሚገኝበት ቦታ ተደርጐ ይቆጠራል
  - የፈጠራ ባለቤትነት፣የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምልክት እና
  - የቅጂ መብት መሰል የሆኑ የአእምሮ ሀብት መብት ማስተላለፍ ወይም ማዛወር፣
  - የምክር፣ የህግ፣ የሂሳብ፣ የምህንድስናና የማስታወቂያ የመረጃ ማጠናቀር እና ሌሎች መሰል አገልግሎቶች፣

## 3.3. አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ

- ❑ የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች አቅርቦት የሚከናወኑበትን ጊዜ ማወቅ አስፈላጊነቱ፤-
  - ታክስ ሪፖርት የሚቀርብበትን ጊዜ፣
  - በግብዓት ላይ የተከፈለው ታክስ ተቀናሽ የሚደረግበትን፣
  - በገዢው ስለሚሰበሰብ ታክስ ደንበኛው ለታክሱ ኃላፊ የሚሆንበትን እና
  - በዜሮ ተመን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የተከናወነበትን ጊዜ ለመወሰን ያስችላሉ

- ከዚህ በታች ከተቀመጡት በህጉ በተለየ ሁኔታ ከተመለከቱት በስተቀር የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች አቅርቦት ተከናወነ የሚባለው ለግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲሰጥ ነው፡፡

➢ ከዚህ በታች ያሉ ድርጊቶች በተከናወኑ በ5 ቀናት ውስጥ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ካልተሰጠ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡

    ✓ ዕቃዎች ለተረካቢው ዝግጁ ሆነው በተቀመጡ፣
    ✓ ሽያጭ ወይም ማስተላለፍ በተፈፀመበት ወይም
    ✓ አገልግሎቶች በሚሰጡበት ጊዜ
    ✓ እንዲሁም የዕቃዎች ርክክብ ማጓጓዝ የሚያካትት ሲሆን የዕቃዎች ማጓጓዝ ሲጀመር፣

➢ ለአቅርቦቱ ግብይት አንድ ወይም ከአንድ የበለጡ ክፍያዎች የተፈፀሙ እንደሆነ በእያንዳንዱ ክፍያ መጠን የተለያዩ ግብይቶች እንደተደረጉ ይቆጠራል

➢ አገልግሎቶች በመደበኛነት ወይም በተከታታይ በሚሰጡበት ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ በተሰጠ ጊዜ፤

➢ ክፍያው አስቀድሞ የተፈፀመ ከሆነ ግን ክፍያው በተፈፀመ ጊዜ፣(ኤሌክትሪክ፣ ስልክ፣. . .)

- ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት ተይዘው ከዚህ ውጪ የዋሉ ዕቃዎችን በተመለከተ

➢ በዕቃው ወይም በአገለግሎቱ መጠቀም የተጀመረበት ጌዜ፣

➢ ቀጣሪ ለተቀጣሪዎች

    • በስጦታ ወይም
    • በሌላ አኳኋን የሚያቀርባቸውን በተመለከተ ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ለተቀጣሪዎች በሚሰጡበት ጊዜ፣

➢ የምዝገባ ስረዛ ሲደረግ በእጅ ያሉ ዕቅዎችን በተመለከተ የምዝገባው መሠረዝ ከሚፀናበት ቀን በፊት ያለው ጊዜ፣

➢ በማሽን ሽያጭ(veneding machin) ግብይት ሲሆን ገንዘቡን ከማሽኑ ሲያወጣ፤

## 3.4. ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እሴት /ዋጋ/

➢ ታክስ የሚከልበት ግብይት እሴት (ዋጋ) የሚሆነው

    ✓ ታክስ ከፋዩ ላቀረባቸው ዕቃዎች ወይም ለሰጣቸው አገልግሎቶች
    ✓ ከደንበኛው ወይም ከማናቸውም ሌላ ሰው የተቀበለውን ወይም ለመቀበል የሚችለው ዋጋ ነው፡፡

- በተጨማሪም የግብይቱ እሴት በአቅርቦቱ ላይ ከተጨማሪ እሴት ታክስ በስተቀር የሚከፈሉ ማናቸውም
  - ✓ ቀረጥ፣
  - ✓ ታክሶች(excise. . .) እና ሌሎች ክፍያዎች ይጨምራል፡፡
- ለተከናወነ አቅርቦት በለውጡ የሚሰጥ ምንም ነገር የሌለ ከሆነ የአቅርቦቱ እሴት የሚሆነው
  - ✓ የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር
  - ✓ ለቀረቡት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማናቸውም ቀረጥ፣ ታክሶች እና ሌሎች ክፍያዎችን ጨምሮ የገበያው ዋጋ ነው፡፡

- ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ የዕቃዎቹ እሴት /ዋጋ/
  - በዕቃዎቹ ላይ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ ጨምሮ
  - በጉምሩክ ህግ መሠረት በጉምሩክ የሚወሰነው የዕቃዎች ዋጋ ነው፡፡
- የዕቃዎቹ እሴት /ዋጋ/ በዕቃዎቹ ላይ የሚጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የገቢ ግብር ቅድሚያ ክፍያ አይጨምርም፡፡
  - ❑ ለጉምሩክ ቀረጥ አወሳሰን በዕቃዎች ዋጋ ውስጥ እስካልተካተተ ድረስ ዕቃን ወደ አገር ከማስገባት ጋር በተንዳኝ ሆነው የተሰጡ አገልግሎቶች እሴት /ዋጋ/ ታክስ በሚከፈልባቸው ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች እሴት ላይ ይጨመራል፡፡(ለምሳሌ የአሳንሰር ግዥ እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ከሆነ ተደምሮ ይጠየቃል…)

**የሙከራ ጥያቄዎች**

- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የምዝገባ ስርዓትን በግልጽ ያብራሩ
- ታክሱ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ስለሚከናወኑበት ቦታ፣ ጊዜና ዋጋ ያረዱ፤

# ክፍል አራት

## 4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማቀናነስ እና ተመላሽ

### 4.1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ

ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ጥቅም ላይ የዋሉበት ወይም የሚውሉበት ለተመዘገበው ሰው የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ሲሆን ታክሱ የሚጣልበት ግብይት የተከናወነበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ ተቀናሽ የሚደረገው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ የተመዘገበው ሰው በቀረበለት የታክስ ኢንቮይስ ወይም ዲክለራሲዮን መሰረት የሚከፍለው ወይም የከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ነው ፡፡

ሀ.የሂሳብ ጊዜ (ዕቃዎች ወደ አገር ገቡ የሚባልበት ጊዜ፤ ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ ገብተዋል የሚባለው በጉምሩክ ዲክላራሲየን ላይ ሲመዘገብ ነው ተብሎ ተጠቅሷል፡፡)

ለ.በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ11 በተመለከተው የሂሳብ ጊዜ እንደተከናወነ በሚቆጠሩ ታክስ የሚጣልባቸው የዕቃ እና አገልግሎት አቅርቦት የከፈለው ታክስ ነው፡፡

ክፍያውን በተመለከተ፤

- በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ የተመዘገበ ሰው ካከናወነው የዕቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከፊሉ  የሆነ እንደሆነ ለዚህ የታክስ ዘመን ተቀናሽ የሚደረገው ታክስ በሚከተለው አኳኋን ይወሰናል፡፡

ሀ.በቀጥታ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የዋለውን  አቅርቦት ወይም ወደ አገር የገባ ዕቃ በሚመለከት ለአቅርቦቱ ወይም ወደ አገር ለገባው ዕቃ የተከፈለው ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ እንደሆን ይደረጋል፡፡

ለ.ከታክሱ ነፃ ለሆነው ግብይት የዋለውን አቅርቦት ወይም ወደ አገር የገባ ዕቃ በሚመለከት ለአቅርቦቱ ወይም ወደ አገር ለገባው ዕቃ የተከፈለው ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡

- ቀጥሎ ለተመለከቱት የተከፈለ ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡

ሀ. አነስተኛ የመንገደኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ያለው ሰው ወደ አገር ላስገባው ወይም በአገር ውስጥ ላከናወነው ግብይት የከፈለውን ታክስ በሚመለከት፤

- እንደዚህ ያሉትን ተሽከርካሪዎች በመሸጥ ወይም በማከራየት የንግድ ሥራ የተሠማራ ወይም ተሽከርካሪውን የገዛው ለንግድ ስራ እንዲውል ካልሆነ በስተቀር ታክሱ እንዲቀናነስ አይደረግም፡፡

- መንገደኞችን በማጓጓዝ የንግድ ተግባር ላይ የተሠማራ ወይም ተሽከርካሪውን የገዛው እና ፈቃድ የተሰጠው ለዚሁ የንግድ ሥራ እንዲውል ካልሆኑ በስተቀር፤

ለ. ከአገር ውስጥ የተገዙት ወይም ወደ አገር የገቡት ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ለመዝናኛ ወይም ለመዝናኛ አገልግሎት የዋሉ በሚሆንበት ጊዜ፤

- ታክስ ከፋዩ በመዝናኛ አገልግሎት ንግድ ስራ ውስጥ የተሰማራ ወይም አቅርቦቱ ወይም ወደ አገር የገባው ዕቃ በንግድ ስራ እንቅስቃሴው ሂደት ታክስ በሚከፈልባቸው የመዝናኛ ስራዎች የሚውል ካልሆነ በስተቀር፤
- ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነ እና የመዝናኛው አገልግሎት ለመንገደኞች የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር፤

➢ **የ 'ሀ' እና 'ለ' መግለጫ**

ሀ "የመንገዶች ማጓጓዣ ተሽከርካሪ" ማለት 8 እና ከ 8 በታች የሆኑ መንገደኞችን ማጓጓዝ የሚችል ተሽከርካሪ ሲሆን ድርብ ጋቢና ያላቸውን ተሽከርካሪዎች ይጨምራል።

ለ "መዝናኛ" ማለት በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ስራ አንድ ክፍል ሆኖ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለማናቸውም ሌላ ሰው የሚቀርብ ምግብ፣ መጠጥ፣ ትምባሆ፣ ማረፊያ፣ መደሰቻ ወይም ማናቸውም አይነት መስተንግዶ ነው።

➢ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ዋጋ ስለማስተካከል

- ግብይቱ ሲሰረዝ፣
- የግብይቱ ተፈጥሮ ሲቀየር፣
- በዋጋ መቀነስም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት አስቀድሞ ለግብይቱ የተጠየቀው ገንዘብ መጠን ሲለወጥ
- ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ በከፊል ወይም በሙሉ ለታክስ ከፋዩ የተመለሱ ሲሆን ነው፣
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የሰጠ እና በደረሰኙ ላይ የተገለፀው ዋጋ የተሳሳተ ሲሆን…
- የተጨማሪ እሴት ታክስ በስራ ላይ ከዋለበት ቀን በኋላ የሚመዘገብ ሰው ከመመዝገቡ በፊት ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ለገዛቸው እና በተመዘገበበት ዕለት በይዞታው ስር ለሚገኙ እቃዎች (የካፒታል ዕቃዎችን ጨምሮ) የከፈለው ወይም ሊከፍል የሚገባው ታክስ በተመዘገበበት ጊዜ ባለው የመጀመሪያ የሂሳብ ጊዜ ተቀናሽ ይደረግባታል።

- አቅርቦቱ ላልተመዘገበ ሰው የሆነ እንደሆነ በብልጫ የታየው ታክስ

- ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ካልተሟሉ በስተቀር በተጨማሪ ዕሴት የታክስ ማቀናነስ ሊደረግ አይችልም፡፡

ሀ/ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ የታክስ ደረሰኝ ወይም የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ሰነድ የተሰጠ እና የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው የታክስ ማስታወቂያ በሚያቀርብበት ጊዜ እነዚህን ደጋፊ ሰነዶች (ደረሰኝ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር) ካላቀረበ የታክስ ማቀናነስ ደንብ ተግባራዊ አይደረግም፡፡

ለ/ የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው ወደ አገር ያስገባውን ዕቃ በሚመለከት የታክስ ማስታወቂያ ሲያቀርብ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ወይም በጉምሩክ ባለስልጣን የተሰጠ ሌላ ሰነድ ካላቀረበ ማቀናነስ አይፈቀድለትም፡፡

- ታክስ የሚከፈልበት ወይም ከታክስ ነጻ የሆነውን የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ለመጀመር ወይም ለማቋረጥ የወጡ ወጪዎች የተፈቀዱ የታክስ ተቀናሾች ስሌት በሚከናወንበት ጊዜ ከግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናል፡፡
- ለመንገደኞች ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች የታክስ ማቀናነስ እንደማይደረግ የተደነገገው በዋነኛነት ዕቃ ለማጓጓዝ የሚውሉ የንግድ፣ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ወይም ሌሎች ተሽከርካሪዎችን አይጨምርም፡፡
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች ወይም ደንበኞች በሬስቶራንት የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ ወይም ሰራተኞች ለመዝናናት ከስራ ቦታቸው ውጭ በሚጓጓዙበት ጊዜ ለመኝታ እና ለምግብ በሚፈፅመው ግዥ ላይ የሚከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ አይፈቀድም፡፡ ይሁን እንጂ የተመዘገበው ሰው "የመዝናኛ አገልግሎት" በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነ (ለምሳሌ ሬስቶራንት) ታክስ ለሚከፈልበት የመዝናኛ ንግድ ስራ በቀጥታ እንዲውሉ በሚገዛቸው የመዝናኛ ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ የተመዘገበ ሰው በተመዘገበ ጊዜ በእጁ በሚገኙ እቃዎች ላይ የተከፈለ ታክስ እንዲቀናነስለት ሊጠይቅ የሚችለው ዕቃዎችን የገዛው ምዝገባው ከፀናበት ቀን በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከሆነ እና እነዚህን ዕቃዎች ከምዝገባው በኋላ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ የሚያውላቸው ከሆነ ነው፡፡

- የተመዘገበ ሰው በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ እንዲቀናነስለት ሊደረግ የሚችለው የታክስ መጠን ድምር በዚሁ የታክስ ዘመን ውስጥ ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ የበለጠ እንደሆነ በብልጫ የሚፈፀም ይሆናል፡፡
- ለታክሱ የተመዘገቡ ሰዎች በአንድ የሂሳብ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ ተቀናሽ እንዲደረግ የተጠየቀው ታክስ ለቀጣዮቹ 5 (አምስት) የሂሳብ ጊዜዎች እንዲተላለፍ ሆኖ በእነዚህ ጊዜዎች ከሚደረግ ክፍያ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡ይህ **የአምስት ወር** ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ቢኖር የተመዘገበው ሰው በብልጫ የተከፈለውን ታክስ ከሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ጋር በማያያዝ ጥያቄውን ባቀረበ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ ሂሳቡን ተመላሽ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም እንዲቀናነስ ሊደረግ የሚችለው የታክስ መጠን ድምር ለአምስት ወር ተከታታይ የታክስ ጊዜ እንደሆነ መረዳት ይችላል፡፡
- በከፊል ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነጻ ለሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደ አገር በገቡ ወይም በአገር ውስጥ በተገዙ ላይ የተከፈለው ታክስ የተመዘገበው ሰው ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሰረት አስልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

ተ = ሀ*ለ/ሐ

ለዚህ ስሌት አፈጻጸም፡-

"ተ"= ተቀናሽ/credit/ ሊደረግ የሚገባ ታክስ

"ሀ"= በከፊል ታክስ በሚከፈልበት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነጻ በሆኑ ግዥዎች ላይ የተከፈለ ጠቅላላ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ፤

"ለ"= የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ነው፡፡

"ሐ"= የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወናቸው ጠቅላላ አቅርቦቶች ዋጋ ነው፡፡

  - ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልባቸው እና ከታሱ ነጻ የሆኑ ግብይቶች የሚያካሂድ ከሆነ የታክሱ ባለስልጣን በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ተቀናሽ የሚደረገው ታክስ ተገቢ መስሎ በታየው ሌላ ስሌት እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>ምሳሌ፡-</u> ሐበሻ ቢራ አክሲዮን ማህበር ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ድርጅት ሲሆን በሀምሌ 2010 ዓ.ም የቢራ ሽያጭ 500,000 ዋጋው ተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር በብር 16 ነው፡፡ ድርጅቱ 500 ኩንታል የቢራ ብቅል ዋጋው ተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር በኩንታል 2000 ብር ከአርሲ ብቅል ፋብሪካ (ለተ.እ.ታ የተመዘገበ) በዚሁ ወር ግዥ ፈፅሟል፡፡ በተጨማሪም አክሲዮን ማህበሩ ለቢራ ማምረቻ የሚሆኑ ኬሚካሎችንና

ሎሌች ጥሬ ዕቃዎችን በብር 100,000 (including C.I.F and other duty excluding VAT) በዛው በተመሳሳይ የታክስ ወር ከውጭ አስገብቷል፡፡

የተጠየቀ፡- የተጠቀሰው ወር የግብዓት ታክስ አቀናንስ?

***መልስ፡***

- የምርት ውጤት ታክስ: 500,000 x 16 x 15%= 1, 200, 000.00
- ሲቀነስ የተከፈለ የግዓት ታክስ :
  - ብቅል፡ 500 x 2000 x 15% =150,000.00
  - ኬሚካል፡ 100,000 x 15% = 15, 000.00
    - ✓ የግብዓት ታስ 165,000.00

**ተከፋይ ታክስ = የምርት ውጤት ታክስ ሲቀነስ የግብዓ ታክስ፡-**

**1200000-165,000 =1, 035,000.00**

| |
|---|
| **ተከፋይ ታክስ/ተመላሽ** = የምርት ውጤት ታክስ - የግብአት ታክስ= **1, 035,000.00** |

## 4.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመላሽ ስርዓት

ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ውስጥ ቢያንስ 25 ፐርሰንት በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ የተመዘገበው ሰው በብልጫ የተከፈለውን ታክስ ከሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ጋር በማያያዝ ጥያቄውን ባቀረበ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የግብር አስገቢው ባለስልጣን በዚህ የሂሳብ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ የተከፈለውን እንዲመልስ የተጠየቀውን ታክስ መመለስ አለበት፡፡

- ሌሎች የተመዘገቡ ሰዎችን በሚመለከት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ ተቀናሽ እንዲደረግ የተጠየቀው ታክስ ለቀጣዮቹ 5 (አምስት) የሂሳብ ጊዜዎች እንዲተላለፍ ሆኖ በእነዚህ ጊዜዎች ከሚደረግ ክፍያ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡ ይህ የአምስት ወር ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ቢኖር የተመዘገበው ሰው በብልጫ የተከፈለውን ታክስ ከሚያሣይ የሰነድ ማስረጃ ጋር በማያያዝ ጥያቄውን ባቀረበ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ ሂሳቡን ተመላሽ ይደረጋል፡፡
- ባለስልጣኑ ለተመዘገበው ሰው ተመላሽ የተደረገው ሂሳብ የተሳሳተ መሆኑን ሲደርስበት ከተገቢው በላይ የተወሰደው ሂሳብ እንዲመለስለት በማናቸውም ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ለተመላሽ ሂሳብ የሚውለውን ገንዘብ፤ ከተሰበሰበው ታክስ ላይ ተቀንሶ የሚያዝበትን ሁኔታ እና በዚህ አይነት የሚያዘውን የገንዘብ መጠን ይወስናል፡፡
- የተመላሽ ጥያቄ ያቀረበው ሰው ሊከፈል ከሚገባው በላይ የከፈለ መሆኑን ሲያረጋግጥ፤

  ሀ) ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን የተመዘገበው ሰው ሊከፍል ከሚገባው ማናቸውም ታክስ፣ቀረጥ፣ወለድ ወይም መቀጫ እንዲውል ይደረጋል፡፡

  ለ) ሊመለስ የሚገባው ታክ መካካስ ለሚገባው ከተካካሰ በኋላ ተመላሽ ሊደረግ የሚገባው ቀሪ ገንዘብ ከብር 50 ያላነሰ ከሆነ ለተመዘገበው ሰው ይመለስለታል፡፡
- የተመዘገበው ሰው ተመላሽ ሊደረግለት የሚገባው ገንዘብ ያለው መሆኑ ተረጋግጦ መመለስ በሚ ገባው ጊዜ ባለስልጣኑ ቀሪውን ገንዘብ ያልመለሰ ከሆነ ተመላሽ እስከሚከፈል ድረስ ባለፈው ሩብ አመት በንግድ ባንኮች ስራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ 25 ፐርሰንት ታክሎበት ለተመዘገበው ሰው እንዲከፈለው ይደረጋል፡፡
- ተመላሽ ሊደረግ የሚገባው ሂሳብ ከብር 50 ወይም ከዚህ በታች ከሆነ ይህ የገንዘብ መጠን ለወደፊት እንዲሸጋገር ተደርጎ በቀጣይ የሂሳብ ዘመን ሊከፈል ከሚገባው ታክስ እንዲታሰብ ይደረጋል፡፡
- ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ጥያቄ የሚያቀርብ የተመዘገበ ሰው ተገቢውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እነደሆነ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው ማስታወቂያውን እስከሚያቀርብ ድረስ ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሳብ ይዞ ለማቆየት ይችላል፡፡

### 4.2.1. የታክስ ተመላሽ የሚፈቀድባቸው ግብይቶች

I. በአንድ የሒሳብ ጊዜ በተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ተፈፃሚ የሚሆነው በሚከተሉት ግብይቶች ነው፡፡

(ሀ) ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ውስጥ ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶ በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ በተከፈለበት ግብይት ላይ በብልጫ የተከፈለ ታክስ ጥያቄው በቀረበ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ ተመላሽ የሚደረገው ለሚከተሉት ግብይቶች ነው፡፡

- ወደ ውጭ የሚላኩ እቃዎች እና አገልግሎቶች፣
- በዓለም አቀፍ በረራ እና ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲሁም ለፍጆታ የሚውሉ የቅባት ዘይቶችና ሌሎች አላቂ የቴክኒክ እቃዎች ግብይት፣
- በአገር ውስጥ አምራቾች ለብሄራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ግብይት፣

(ለ) በካፒታል እቃዎች ላይ በተደረጉ ግብይቶች እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሰው በሚያስቀሩ አካላት ተቀናሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽን ሳይጨምር ተመላሽ መደረግ ያለበት ታክስ በታክስ ጊዜው ውስጥ ያልተቀናነሰ እንደሆነ በሚቀጥሉት አምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከሚከፈለው ታክስ ላይ የሚቀናነስ ሆኖ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያልተቀናነሰ ቀሪ ሂሳብ ያለ እንደሆነ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአርባ አምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

ሐ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በሚያስቀር ሰው ታክስ ተቀንሶ የተከፈለበት ደረሰኝ የተሰጠው ታክስ ከፋይ በተቀበለው ደረሰኝ ላይ የተገለፀውን የታክስ መጠን በግብዓት ላይ ከተከፈለው ታክስ ጋር እንዲያካክስ በማድረግ ቀሪው ሂሳብ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአርባ አምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

(I) ታክስ ከፋዩ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በቋሚ የንግድ ስራ እቃ ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲቀናነስ የተፈቀደ እንደሆነ በሂሳብ ጊዜው በግብዓት ላይ ከተከፈለው ታክስ ላይ እንዲቀናነስ ተደርጎ ቀሪው ሂሳብ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

(II) አንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የንግድ ስራውን በማስፋፋት ሂደት ግንባታው ባልተጠናቀቀ ህንፃ ላይ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ህንፃው ተጠናቆ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ተግባር መዋሉ ሲረጋገጥ በግብዓቱ ላይ የተከፈለው ታክስ (In put tax) በግብይት ላይ ከተከፈለው ታክስ (Out put tax) ላይ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ እንዲቀናነስ ተደርጎ ቀሪው ሂሳብ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ በአርባ አምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

(ሠ) ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጪ ያለው ፕሮጀክት ለፕሮጀክቱ ግብዓት በዋለ ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲመለስለት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ግዥው ከተከናወነበት ቀን ቀጥሎ ባለው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

(ረ) በማእድንና ነዳጅ ፍለጋ የተሰማራ ኩባንያ የማእድንና ነዳጅ ፍለጋው ሳይሳካለት የቀረ እንደሆነ ከማእድን ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲያቀርብ በግብዓት ግዥ ላይ ለከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ማስረጃ በማያያዝ የታክስ ተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ የሚችል ሲሆን ተመላሽ መደረግ ያለበት ታክስ ተረጋግጦ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

(ሰ) በውጭ ንግድ ማበረታቻ አዋጅ በተደነገገው መሰረት በተፋጠነ የተመላሽ ስርዓት እንዲስተናገድ የተፈቀደለት ላኪ ምርቱን ወደ ውጭ ከመላኩ በፊትም ቢሆን በሃገር ውስጥ ባከናወነው የግብዓት ግዥ ላይ ለከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይቱ ከተከናወነበት ቀን ቀጥሎ ባለው ወር ውስጥ የተመላሽ ጥያቄውን ካቀረበ በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

(ሸ) የባለ ልዩ መብት ድርጅት ለድርጅቱ አገልግሎት በሚውል እቃ ላይ የከፈለው ተጨማሪ አሴት ታክስ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

(ቀ) የበጎ አድራጎት ድርጅት ለተረጂዎች ጥቅም በሚውል እቃ ወይም አገልግሎት ላይ የከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

(በ) ለኮንደሚኒየም ቤቶችና ለመከላከያ ፋውንዴሽን ግንባታ ጥቅም ላይ በዋለ ግብዓት ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲካካስ ይደረጋል፡፡

(ተ) ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፈቃድ በመውሰድ የካፒታል እቃዎች የሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ለማቅረብ ከአገር ውስጥ አምራቾችና አስመጪዎች የካፒታል እቃውን ሲገዙ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

II/ በከፊል ታክስ ለሚከፈልበት እና በከፊል ከታክስ ነፃ ለሆነ ግብይት በዋለ እቃ እና አገልግሎት ላይ የተከፈለ ታክስ፡-

(ሀ) ለታክሱ የተመዘገበ ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ለጠቅላላ ግብይት ዋጋ ሲካፈል ከዘጠና በመቶ በላይ ከሆነ በግብዓቱ ላይ የተከፈለውን ታክስ ሙሉ ለሙሉ በማቀናነስ ቀሪ ሂሳብ መኖሩ ሲረጋገጥ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

(ለ) ለታክሱ የተመዘገበ ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ለጠቅላላ የግብይቱ ዋጋ ሲካፈል ውጤቱ ከዘጠና በመቶ በታች ከሆነ በግብዓቱ ላይ የተከፈለው ታክስ ተመላሽ አይደረግም፡፡

## 4.2.2.መደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስርዓት አፈፃፀም

1. በሚኒስቴሩ የሚሰጥ መደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አገልግሎት እና የሚከናወን የቁጥጥር ስርዓት በመረጃ በተደገፈ የስጋት መምርጫ መስፈርት የታክስ ከፋዩን የሥጋት ደረጃን በመለየት የሚከናወን ይሆናል፡፡
2. ስጋትን መሰረት ያደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ አገልግሎት ተግባራዊ የሚደረገው በመደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስርዓት ነው፡፡
3. ሚኒስቴሩ መደበኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽን በሚመለከት የሥጋት ደረጃን የሚወስን የአሰራር ማኑዋል አለው፡፡
4. ታክስ ከፋዩ የተመዘገበው በግብር ዘመኑ በመሆኑ ምክንያት መረጃ ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ የታክስ ተመላሽ አገልግሎት የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ፡-

ሀ) ለአቅራቢያው በባንክ በኩል ክፍያ የፈፀመበትን ማስረጃ ካቀረበ፣ ወይም

ለ) ተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው ክፍያ የፈፀመለት በባንክ በኩል መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካቀረበ የተመላሽ ጥያቄው <u>በአነስተኛ ኦዲት ተጣርቶ</u> ተመላሽ ይደረጋል፡፡

5. ለግብይቱ ክፍያ የተፈፀመው በባንክ በኩል ካልሆነ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ተመላሽ ጥያቄ በከፍተኛ ኦዲት ተጣርቶ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

ሀ) በአነስተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደብ እና ኦዲት ሳይደረግ ተመላሽ የሚደረግለት ታክስ ከፋይ የተመላሽ ጥያቄ ባቀረበ <u>በሰባት ቀን ውስጥ</u> ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

ለ) በአነስተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደብ እና ኦዲት ከተደረገ በኋላ ተመላሽ የሚፈፀምለት ታክስ ከፋይ የተመላሽ ጥያቄውን ባቀረበ <u>በሰላሳ ቀን ውስጥ</u> ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

## 4.2.3. ከተ.እ.ታ ነፃ በተደረገ ሰው ላይ የሚፈፀም የታክስ ተመላሽ ሥርዓት

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መብት ያለው ሰው በአገር ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሲያከናውን ታክሱን ከፍሎ በተመላሽ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡
- የታክስ ነፃ ባለመብቱ ለአቅራቢው ክፍያ የፈፀመው በባንክ በኩል መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካቀረበ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ <u>**በሰባት ቀናት ውስጥ**</u> ተመላሽ ይደረጋል፡፡
- የታክስ ነፃ ባለመብቱ ለአቅራቢው ክፍያ የፈፀመው በባንክ በኩል ካልሆነ በአነስተኛ ኦዲት ተጣርቶ የተመላሽ ጥያቄው በቀረበ **በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ** ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## 4.2.4.የታክስ ተመላሽ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- **የተመላሽ መጠየቂያ ቅጽ ስለመሙላት እና ማስረጃ ስለማቅረብ**

1/የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የተመላሽ ጥያቄውን በሚያቀርብበት ጊዜ የሚጠበቅበትን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ጥያቄውን የታክስ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የተመላሽ መጠየቂያ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት።

2/የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት የሚጠይቅ ማንኛውም ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ከተሞላው ቅፅ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት።

ሀ) በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ከተከናወነው ግብይት መካከል ቢያንስ ሃያ አምስት በመቶ የሚሆነው ግብይት እቃን ወደ ውጭ በመላክ የተከናወነ ግብይት ከሆነ ወደ ውጭ የተላከውን እቃ መጠን እና እቃው ለውጭ ገበያ የተላከ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ፣

ለ) በፊደል "ሀ" መሠረት የሚቀርበው ማስረጃ የሚከተሉትን የሚጨምር ይሆናል።

1.ለማስጫኛ ወይም ለትራንስፖርት ክፍያ የተፈፀመበት ሰነድ (Bill of loading Air way Bill)

2.ዕቃው ወደ ውጭ የተላከበት የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፣

3.የባንክ ፈቃድ (Bank permit),

4. ሽያጩ የውጭ ምንዛሪ ያስገኘ መሆኑን የሚያሣይ ሰነድ (Bank Credit Advice),

5.ወደ ውጭ ለተላከው እቃ ግብዓት የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያሳይ የድርሻ ስሌት ሰንጠረዥ፣

6.ዕቃው ከተላከለት ገዥ ጋር የተደረገውን የዕቃ ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ውል፣

ሐ) በዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት የተሰማራ ሰው ከሆነ በሂሳብ ጊዜው ከትራንስፖርት አገልግሎቱ ጋር በቀጥታ ለተያያዙ ግብዓቶች የተከፈለ ታክስ መኖሩን የሚያሣይ ህጋዊ ደረሰኝ እና ማስረጃ፤

መ) ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ወርቅ የሚያቀርብ የአገር ውስጥ ወርቅ አቅራቢ በተሰጠው የሒሳብ ጊዜ ላከናወነው አቅርቦት ከብሄራዊ ባንክ የተሰጠ ማስረጃ እና ወርቁን ለማቅረብ የተከፈለ የግብዓት ታክስ ያላቸው መሆኑን የሚያሣይ የታክስ ደረሰኝ እና ሌሎች ማስረጃ፤

ሠ) በፊደል (ሀ) እና (ለ) የተገለፀው ቢኖርም በተፋጠነ የተመላሽ ስርዓት የሚስተናገድ ታክስ ከፋይ ምርቱን ወደ ውጭ ከመላኩ በፊትም ቢሆን በግብዓት ላይ የከፈለው ታክስ

ተመላሽ እንዲደረግለት የተፈቀደበትን ማስረጃ እና በአገር ውስጥ የግብዓት ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፣

ረ) በመደበኛ 15 በመቶ የማስከፈያ ልክ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚጠይቁ ታክስ ከፋዮች ከተሞላው የተመላሽ ቅጽ ጋር የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለባቸው፡፡

1.ታክስ የተከፈለበት ግብዓት በምርት ሂደት ጥቅም ላይ መሆኑን የሚያስረዳ የምርት ጥመርታ ማስረጃ (input out put coefficient)

2.የተሸጠ ምርት ወይም እቃ እና ያልተሸጠ ወይም በመጋዘን የሚገኝ የስቶክ ማረጋገጫ ማስረጃ፣

3. በገዥው ተይዞ የሚከፈል ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ከወኪሎች ጋር የተደረገውን የግብይት መጠን የሚያሳይ ማስረጃ እና ከወኪሉ የተቀበለውን ኦርጂናል ደረሰኝ ለታክስ ባለስልጣኑ ያስረከበ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

4. በማዕድንና ነዳጅ ፍለጋ ላይ የተሰማራ ኩባንያን በተመለከተ ድርጅቱ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር በሚጽፈው የታክስ ተመላሽ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

5.በከፍተኛ ኢንቨስትመንት የተሠማራ ባለሃብትን በተመለከተ ከአንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡ መሆኑን የሚገልፅ ከብሄራዊ ባንክ የተሰጠ ማረጋገጫ ወይም የፕሮጀክቱ ወጪ ከአንድ መቶ ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር በላይ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የኦዲት ሪፖርት እንዲሁም ፕሮጀክቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት እስኪ ጀምር ሶስት አመት እና ከዚያ በላይ የሚወስድበት መሆኑን የሚያሥረዳ ማስረጃ፣

(ሰ) ከህንፃ ውጪ ባለ በቋሚ ዕቃ ግዥ ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግ ጥያቄ የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከመመዝገቡ በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ወይም በሂሳብ ጊዜው ለተገዛ ዕቃ ለተከፈለ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ እና በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የዋለ መሆኑን እና በድርጅቱ የተመዘገበ ቋሚ ዕቃ መሆኑን የሚያሥረዳ ማስረጃ፣

(ሸ) በአዲስ ህንፃ ግንባታ ወይም በማስፋፊያ ግንባታ ጊዜ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግ የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ፤

1. ለታክሱ ከተመዘገበ በኂላ ለአዲስ ህንፃ ግንባታ ወይም ማስፋፊያ በዋለ ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበትን ደረሰኝ፣

2. ህንፃው የተሠራው በህንፃ ተቋራጭ ከሆነ የህንፃ ተቋራጩ በሚያቀርበው የግብዓት ዋጋ ዝርዝር መሠረት የተከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን የሚያሣይ ደረሰኝ፣

3. ህንፃው የተጠናቀቀ እና ስራ መጀመር የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ስልጣን ከተሰጠው የመንግስት ተቋም የተሰጠ ማስረጃ፣

ቀ/ የባለ ልዩ መብት ተጠቃሚ ድርጅት የታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ሲጠየቅ የሚከተሉትን ማስረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ) ባለ ልዩ መብቱ የገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ለተቋሙ ስራ ማስፈፀሚያ (Official use) የዋለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ኃላፊነት በተሰጠው የተቋሙ የስራ ኃላፊ ማረጋገጫ፣

ለ) በሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ የተረጋገጠ የእቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ደረሰኝ፣

ሐ) ባለ ልዩ መብቱ ክፍያ የፈፀመው በባንክ ከሆነ ክፍያው የተፈፀመበትን የባንክ አካውንት፣

መ) ባለ ልዩ መብቱ ያቀረበው የተመላሽ ጥያቄ ከግንባታ ጋር የተያያዘ ከሆነ የግንባታ ስራ ውሉንና ለስራ ተቋራጩ የታክስ ክፍያ የፈፀመበትን የታክስ ደረሰኝ፣

በ/ የበጎ አድራጎት ድርጅት የታክስ ተመላሽ ሲጠይቅ የሚከተሉትን ማስረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

5. በበጎ አድራጎት ድረጅትና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ፤
6. የዘመኑ የታደሰ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤
7. የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለተረጂዎች የዋለ ስለመሆኑ በኤጀንሲው የተረጋገጠ ማስረጃ፤
8. በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሒሳብ ሪፖርት፤
9. ለእርዳታ የሚውል ፕሮጀክት ለማከናወን የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማስመለስ ከሆነ ታክስ የተከፈለበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ጥቅም ላይ የዋለ ስለመሆኑ በኤጀንሲው የተረጋገጠ ማስረጃ፤

10. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የውጭ አገር ድርጅት ከሆነ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዕውቅና ያገኘበትን ማስረጃ፤

ተ/ ለኮንደሚኒየም ቤቶች እና ለመከላከያ ሰራዊት ፋውንዴሽን ግንባታ በዋለ ግብዓት ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚደረገው እንደ ሁኔታው የክልሉ ወይም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የመከላከያ ሚኒስቴር የሚከተለውን ማስረጃ አሟልተው ሲቀርቡ ይሆናል፡፡

- የክልል መስተዳድሮች እና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም የመከላከያ ፋውንዴሽን ለሚያስገነቧቸው የኮንደሚኒየም ቤቶች በአገር ውስጥ በተፈፀመ የግብዓት ግዥ ላይ የከፈሉት ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ በእያንዳንዱ ወር ግብይት ላይ ለተከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ የተጠቃለለ የታክስ ደረሰኝ ከኦርጂናሉ ጋር በማገናዘብ እና ማህተም በማድረግ ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ጥያቄው በተመላሽ መጠየቂያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ እንደሁኔታው የክልሉ እና የከተማ አስተዳደሩ የቤቶች ልማት ኤጀንሲ እንዲሁም የመከላከያ ፋውንዴሽን የበላይ ኃላፊ ወይም እነዚሁ በሚወክሏቸው የስራ ኃላፊዎች ተፈርሞ መቅረብ አለበት፡፡

ቸ/የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት የሚያቀርቡ የፋይናንስ ድርጅት በሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎች ከአገር ውስጥ አምራቾች ወይም አስመጪዎች ሲገዙ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚደረገው የሚከተለው ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ ነው፡፡

- የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት ደረሰኝ
- ከኢትዮጵያ በሄራዊ ባንክ የተሰጠ የሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ፈቃድ፤
- የሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ሰጪው ከተከራዮች ጋር ያደረገውን ውል፤

- ❑ ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ፈቃዱ ከተሰረዘ በኋላ በሚያከናውነው ግዥ ላይ ለከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡
- ❑ ለህንፃ ግንባታ በሚውል ግብዓት ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚደረገው የህንፃው ግንባታ ተጠናቆ ገቢ ማመንጨት በተጀመረበት የመጀመሪያው የሒሳብ ጊዜ ከሰበሰበው ታክስ ላይ እንዲቀናነስ ከተደረገ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ካለ ታክስ ከፋዩ ገቢ ማመንጨት ከጀመረበት ወር ቀጥሎ ባለው ወር ውስጥ ይሆናል፡፡
- ❑ ለህንፃው ግንባታ በዋለ ግብዓት ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ግንባታው ተጠናቆ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ማመንጨት ከመጀመሩ በፊት በተደረጉ ሌሎች ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ ከተሰበሰበ ታክስ ጋር ሊቀናነስ አይችልም፡፡

- ማንኛውም የተመዘገበ ታክስ ከፋይ በግብዓት ላይ የከፈለው ታክስ የካፒታሉ አካል ሆኖ ከተመዘገበ እና የእርጅና ቅናሽ ወጪ እንዲታሰብለት ከተደረገ ታክሱ ተመላሽ አይደረግም፡፡
- የልዩ መብት ተጠቃሚ የታክስ ተመላሽ ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ የልዩ መብት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ለታክስ ባለስልጣኑ መላክ አለበት፡፡
- ባለ ልዩ መብቶች ለገዙት ዕቃ ወይም አገልግሎት ክፍያ የፈፀሙት ከNT ወይም ከNR አካውንት ላይ ከሆነ ታክሱ ተመላሽ የሚደረገው ገንዘቡ ወጪ በተደረገበት አካውንት መልሶ በማስገባት ነው፡፡
- ማንኛውም ባለ ልዩ መብት በዕቃ ወይም በአገልግሎት ግዥ ላይ የከፈለው ታክስ ተመላሽ የሚደረገው የተመላሽ ጥያቄውን ባቀረበ <u>በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ</u> ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ ለግብይቱ ክፍያ ከተፈፀመ <u>ከአንድ አመት በኋላ</u> የሚቀርብ የታክስ ተመላሽ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

### 4.2.5. የልዩ ባለመብቶች የሚከፍሉት አገልግሎት ክፍያ ከታክሱ ነፃ ስለመደረጉ

- የልዩ መብት ተጠቃሚዎች በሚከፍሉት <u>የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት</u> ክፍያ እና <u>የህንጻ ኪራይ</u> ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል የለባቸውም፡፡
- የልዩ መብት ተጠቃሚው የሕንፃ ኪራይ በሚከፍልበት ጊዜ ከታክስ ባለስልጣኑ የተሰጠውን የታክስ ነጻ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ኮፒ በማድረግ እና በማህተም በማረጋገጥ ለአከራዩ መስጠት አለበት፡፡

**ምሳሌ፡-**ጊዮን ጫማ ፋብሪካ ለተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ሲሆን 10,000 ኪ.ግ ቆዳ ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ (ለተ.እ.ታ ተመዝጋቢ) ቫትን ጨምሮ በኪሎ 690 ብር ገዛ ፡፡በተጨማሪም ለጫማ ምርት የሚሆን ኬሚካል እና ሌሎች ጥሬ ዕቃዎች በብር 400,000 (C.I.F እና ሌሎች ቀረጦች ቫትን ሳይጨምር) ለህዳር ወር ምርት የሚሆን ከውጭ አስገብቷል፡፡ ጊዮን ፋብሪካ ደረጃውን የጠበቀ የ 3 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው ጫማ ወደ ካናዳ እና ህንድ እንዲሁም 20,000 ጫማ ቫትን ሳይጨምር በጫማ 300 ብር ለሀገር ውስጥ ገበያ ሸጠ፡፡

***<u>ጥያቄ፡-</u>*** የወሩን ቫት አቀናነስ

***<u>መልስ</u>***

a. የምርት ውጤት ታክስ
b. ወደአገር ውሥት የገባ 20,000x300x15%
   900,000.00

c. ወደውጭ የተላከ፡ 3,000,000x0%
   0.00
d. ሲቀነስ: ለግብአት የተከፈለታክስ :
e. ሌዘር 10,000x690x15/115 900,000.00
f. ኬሚካል 400,000x15/100 60,000.00
g. አጠቃላይ የተከፈለ የግብዓት ታክስ : 960,000.00
h. **ተመላሽ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ : 60,000.00**

| **ተመላሽ የተጨማሪ ዕሴት ታስ** = የምርት ውጤት ታክስ - የግብአት ታክስ |
|---|

ከላይ እንደተገለፀው 60,000.00 ብር በአብላጫ የተከፈለ የግብዓት ታክስ የወሩ ክሬዲት ሲሆን እስከሚቀጥለው 5 ተከታታይ ወር ማቀናነስ የሚችል ሲሆን 5 ወራት ውስት ካልተጣፋ ግን ጊዮን ጫማ ፋብሪካ ተመላሽ ጠይቆ በባለስልጣኑ ይመለስለታል፡፡

## 4.2.6. በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ

### ❑ ታክስ በሚከፈለበት ግብይት ዋጋ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ስለሚያዝ ታክስ

ማናኛውም ወኪል ለአቅራቢው መክፈል ካለበት ታክስ ውስጥ 50% ቀንሶ በመያዝ ለገቢ መስሪያ ቤቱ ገቢ ማደረግ አለበት፡፡ ቀሪውን 50 % ለአገልግሎት አቅራቢው መከፈል አለበት፡፡ ከዕቃ/የአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ የሚቀረው ታክስ በቅድመ ክፍያ ግዜ እና በከፊል ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይም ይቀነሳል፡፡ ክፍያው የተፈፀመው በዶላር ከሆነ በባንክ በኩል ወደ ብር ተቀይሮ በተቀየረበት መጠን ላይ ታክስ ይሰበሰባል፡፡ ሜጋ ፕሮጀክቶችን የሚያከናውኑ የመንግስት የልማት ድረጀት ከሚፈፅሙት ክፍያ ላይ ታክስ ቀንሰው የሚያስቀሩት የአገልግሎት ዋጋ ነው ተብሎ በሚወሰደው 50% ላይ ብቻ ነው፡፡

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር በብድር ባገኙት ገንዘብ ለሚከናወን ፕሮጀክት ክፍያ የሚፈፀመው በአበዳሪው አካል ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡

በቴሌ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ በገዥው አይያዝም፡፡

### ❑ ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት የግብይት ዋጋ

- ወኪሉ ከብር 200,000 ብር በላይ ዋጋ ያለው ዕቃ /አገልግሎት ሲገዛ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበ ግብር ከፋይ መሆን አለበት፡፡

- ለታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ከ 20,000 በላይ ሲሆን ወኪሉ የታክሱን 50% ቀንሶ ማስቀረት አለበት፡፡ ነገር ግን በአንድ ጊዜ የሚከፈለው ክፍያ 20,000 እና በታች ከሆነ የታክሱን ሂሳብ ጨምሮ ለታክስ ከፋዩ መክፈል አለበት፡፡
- በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው/ድርጅት የሚሰጥ አገልግሎት የገንዘቡ መጠን /20000/ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ታክሱ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

### 4.2.7.የወኪሉ ግዴታ

- ታክሱን ቀንሶ ለማስቀረት ውክልና የተሰጠው አካል በባለስልጣኑ ተመዝግቦ ቲን ሰርቲፊኬት መያዝ አለበት፡፡
- በእያንዳንዱ ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ላይ 50% ቀንሶ የመያዝ፤
- ቀንሶ በሚይዘው ታክስ መጠን ልክ በገኘው ተይዞ የሚከፈል ለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የመስጠት
- በሚፈፅመው ክፍያ ከዕቃ/ከአገልግሎት አቅራቢው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የመቀበል
- ቀንሶ የያዘውን ታክስ ወሩ በተጠናቀቀ በቀጣዩ ወር በ30 ቀን ውስጥ ለገቢ መስሪያ ቤቱ ገቢ ማድረግ
- ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ጋር ተያይዞ ክፍያ የተፈፀመለትን አካል ዝርዝር የታክስ መረጃዎችን ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ
- በግብይት የሚከፈለው ታክስ ለአቅራቢው የሚከፈል/ተቀንሶ የተያዘ ታክስ ከሌለ ወሩ ከተጠናቀቀ በቀጣይ 30 ቀናት ውስጥ ለገቢ መስሪያ ቤቱ በደብዳቤ ማረጋገጥ አለበት፡፡
- ወኪሉ ታክሱን በትክክል ቀንሶ ያላስቀረ እንደሆነ/ የቀነሰውን ታክስ ለገቢ መስሪያ ቤቱ ገቢ ያላደረገ እንደሆነ ወኪሉ የሚከፍለውን ታክስ ወለድ እና መቀጫውን ጨምሮ እንድከፍል ይደረጋል፡፡
- ወኪሉ የዕቃ/አገልግሎት አቅራቢው ደረሰኝ በሰጠበት ወር በገኘው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካልሰጠው መስጠት ከነበረበት እና እስከ ሰጠበት ባለው ጊዜ ውስጥ ወለድና ለዘገየበት ቅጣት እንድከፍል

**የሙከራ ጥያቄዎች**

- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ በምሳሌ ያስረዱ፤
- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ የሕግ አግባቡን በማስረዳት ተመላሽ የሚፈቀድባቸውን ግብይቶች ይለዩ፤

ክፍል አምስት

# 5. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ማሳወቅ እና ስረዛ

## 5.1. ማሳወቅ

በማንኛም በ12 ወር ጊዜ ውስጥ የተከናወነ ጠቅላላ ሽያጭ **ብር ሰባ ሚሊዮንና ከዚህ በላይ** ከሆነ ታክስ ከፋዩ **በእያንዳንዱ ወር** ማስታወቂያ የሚያቀርብ ሲሆን በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ ሽያጭ **ከብር ሰባ ሚሊዮን በታች** የሆነ ታክስ ከፋይ ሦስት ወር ሲሆን የነሐሴና የጳጉሜ ወራት እንደ አንድ ወር ይቆጠራል ::

## 5.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ስረዛ ጊዜና ሥርዓት

ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ያለው **የሦስት ዓመት** ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት 12 ወራት ውስጥ በሰርኩላሩ የተሻሻለው ለታክሱ የግዴታ ምዝገባ ከተቀመጠው አመታዊ ታክሱ የሚከፈልበት የግብይት ዋጋ የማይበልጥ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

በዚሁ መሰረት ለታክሱ የተመዘገበ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ታክስ የሚከፍልበትን ግብይት ወይም የንግድ ሥራ ለማቆም ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ምዝገባው እንዲሰረዝለት የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የፅሁፍ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡-

- ታክስ ከፋዩ ግብይቱን ያቋረጠበት ቀን
- ታክስ ከፋዩ ግብይቱን ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለማከናወን ያቀደ መሆን ያለመሆኑን የሚገልየፅ

ምዝገባውን ለመሰረዝ የታክስ ባለስልጣኑ ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፍልበትን ግብይት ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ ባለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያከናውናል ለማለት በቂ ምክንያት ከሌለው የስረዛ ማመልከቻውን በመቀበል ግብይቱ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ይሰርዛል፡፡ ነገር ግን የታክስ ባለስልጣኑ ታክስ ከፋዩ ምዝገባውን ካከናወነበት ቀን ጀምሮ ታክሱ የሚከፈልበትን ግብይት ያለመፈፀሙን ካረጋገጠ ወደ ኋላ በመመለስ ምዝገባው ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሰረዝ ማድረግ ይችላል፡፡

በታክስ መስሪያ ቤቱ አማካኝነት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተደረገ ምዝገባ በተሰረዘ ጊዜ የተመዝጋቢውን ስም እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ከተጨማሪ እሴት ታክስ መዝገብ የሚሰርዝ ሲሆን ተመዝግቦ የነበረው ሰውም የተሰጠውን የምዝገባ ሰርተፊኬት ይመልሳል፡፡

### 5.3. በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ስረዛ ጊዜ ስለሚታሰብና ስለሚቀናነስ ታክስ

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄ ሲቀረብ ታክስ ከፋዩ በእጁ የሚገኙ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እና የካፒታል እቃዎች ታክስ በሚከፈልበት የግብይት ዋጋ እንደተሸጡ ይቆጠራሉ፡፡ ያማለት ታክስ ከፋዩ ባልተሸጡት እቃዎች ላይ የሚመለስለትም ሆነ የሚከፍለው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የለም፡፡

- ❖ በተመሳሳይ በንግድ ስራ ሃብትነት በተያዙ የካፒታል እቃዎች ላይም የተያዘ ክሬዲት ሊቀናነስ የሚችለው እያንዳንዱ ቋሚ እቃ የተገዛበትን ዋጋ እና ጊዜ በተናጠል ለይቶ በማስላት ይሆናል፡፡

I. **የካፒታል እቃዎች የአገልግሎት ዘመን፡፡**

ሀ. የኮምፒዩተርና የሶፍትዌር ውጤት 4 ዓመት

ለ. ሌሎች ማናቸውም የንግድ ስራ ቋሚ ንብረቶች 5 ዓመት

ሐ. የህንፃዎች 20 ዓመት ይሆናሉ፡፡

3) የካፒታል እቃ ቀሪ ዋጋ ስሌት

ሀ/ የካፒታል እቃ ቀሪ ዋጋ ላይ ለመድረስ የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ ይሰላል፡-

$$\left(-\frac{\text{ሀ}}{\text{ለ}} x\text{ሐ}\right) = \text{መ}$$

<u>መግለጫ፡-</u>

ሀ= የንብረቱ ቀሪ የአገልግሎት ዘመን

ለ = የንብርት ጠቅላላ አገልግሎት ዘመን

ሐ= የካፒታል እቃው ወጪ /ዋጋ/ acquisition cost/ Book value/

መ= የካፒታል ዕቃው ቀሪ ዋጋ

ለ/ የሚከፈል ወይም የሚቀናነስ ታክስ አሰላልን በተመለከተ ከላይ የተመለከተውን መግለጫ መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**ሠ=መ** x 15%

<u>መግለጫ፡-</u> ሠ= የሚከፈል/የሚቀናነስ ታክስ

መ= የካፒታል ዕቃው ቀሪዋጋ

በዚህ ቀመር መሰረት ተሰርቶ የተገኘው ታክስ (ሠ) ከተጠየቀው ወይም ከተያዘው ክሬዲት እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡

**የሙከራ ጥያቄዎች**

- ➢ ከተጨማ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ለመሰረዝ የሚያበቁ መስፈርቶችን ይዘርዝሩ

## ክፍል ስድስት

# 6. ከተጨማሪ ዕሴት ጋር የተያያዙ አስተዳራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

## 6.1. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- በጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት ለጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሰው ሳይመዘገብ የቀረ እንደሆነ፤ መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገብ እስካመለከተበት ወይም በባለስልጣኑ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ወር ወይም ከወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር 2 ሽህ (ሁለት ሽህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
- በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ፤ ንዑስ አንቀፁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ሰው መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገብ እስካመለከተበት ወይም በባለስልጣኑ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በፈፀመው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ 100 % (መቶ በመቶ) ቅጣት ይከፍላል፡፡
- በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት የሚጣለው ቅጣት በንዑስ አንቀፁ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ በፈፀመው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አያስቀርም፡፡ ሆኖም ታክስ ከፋዩ በዚህ ጊዜ ውስጥ ባከናወነው ግብይት ላይ የከፈለው የተርን ኦቨር ታክስ ካለ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡
- ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሳነስ ወይም በግብቱ ላይ ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ እንደሆነ ብር 50 ሽህ (ሃምሳሽህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፡፡
- ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥ ባልሰጠው ለእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 50 ሽህ (ሃምሳ ሽህ) ቅጣት ይከፍላል፡፡
- በታክስ ማስታወቂያ የተገለጸው የታክስ መጠን ታክስከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ትክክለኛ የታክስ መጠን ያነሰ እንደሆነ ( “የታክስ ጉድለት” ልዩነት እና የልዩነቱን መጠን በ10% ይቀጣል፡፡ይህንኑ ከደጋገመ ልዩነቱን ከ30-50% ይከፍላል፡፡

## 6.2. የወንጀል ቅጣቶች

- ባለስልጣኑን ለማጭበርበር በማሰብ ያለአግባብ ተመላሽ ወይም ማካካሻ የጠየቀ ሰው ብር 50 ሽህ (ሃምሳ ሽህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት

በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል። የሚጣለው ቅጣት ታክስ ከፋዩ ተመላሽ የተደረገለትን ታክስ መልሶ ከመክፈል ግዴታ ነፃ ሊያደርገው አይችልም።

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይመዘገብ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ ሰው ብር 200 መቶ ሽህ (ሁለት መቶ ሽህ ብር ) የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው፤

ሀ/ በተ.እ.ታ አዋጅ መሰረት የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ

ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ከተፈቀደው ውጭ የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ የሰጠ እንደሆነ፤ብር 10 ሽህ (አስር ሽህ) የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል ዕስራት ይቀጣል።

ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠወይም ያሰራጨ፤ወይም

ለ/ የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ ወይም ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የተጠቀመ እንደሆነ፤ብር100 ሺ የገንዘብ ቅጣት እና ከ7-10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

- ሀሰተኛ ደረሰኞችን፣ ለማዘጋጀት/ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሳሪያ፣ ወይም ሶፍት ዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ፣ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ብር 200ሺ የገንዘብ ቅጣት እና ከ 10-15 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።
- ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ፣ ወይም ሀሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሰው ከ3-5 ዓመት በሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡
- ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ ወይም የተቀበለ ሰው ከብር 100 ሺ እስከ ብር 200 ሺ ቅጣት እናከ 7-10 ዓመት በሚያደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።
- ማንኛውም ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከብር 100-200 ሺ ቅጣት እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።
- ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ቀንሶ የያዘውን ታክስ ለመንግስት ያላስተላለፈ ከሆነ ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

**ማስታወሻ፡-** የሁሉም ታክሶች እስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት ህግ በአንድ ላይ ተጠቃሎ በአዋጅ 983/2008 ቢኖርም ለዚህ ሰነድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 በአንቀፅ 30(3)፣(4)፣(5) እና በአንቀፅ 50 (ሀ)፣(ለ)፣(ሐ) ላይ የተገለፁ ቅጣቶችን በተጨማሪነት ማየት ያስፈልጋል፡፡

**የሙከራ ጥያቄዎች**

- ከተጨማ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ለመሰረዝ የሚያበቁ መስፈርቶችን ይዘርዝሩ
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች ይለዩ፡፡

**ማጠቃለያ**

በአጠቃላይ፣ ሞጁሉ ስድስት ክፍሎች የተጨማሪ እሴት ታክስ የተዳሰሰ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ ሁኔታ ቀርቧል፡፡ በሁለተኛው ክፍል የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባና ስረዛን የሕግ መሠረትና ታሳቢዎች፣ ይዘትና አፈጻጸም የያዘ ነው፡፡ በክፍል ሦስት የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ የሕግ መሠረት፣ ታሳቢዎች፣ ይዘትና አፈጻጸም

ተቀምጠዋል። ክፍል አራት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሕግ መሠረት፣ ይዘትና አፈጻጸምን ሲያካትት ክፍል አምስት በገኘው ተይዞ ስለሚከፍል የተጨማሪ እሴት ታክስ መመሪያ ዝርዝር ይዘትና አፈጻጸም እንዲሁም በክፍል ስድስት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ተያያዥ የሆኑ አስተዳደራዊና ወንጀል ቅጣቶችን አካቷል። በመሆኑም እነዚህን የተጨማሪ እሴት ታክስ ድንጋጌዎች በመከተል ግዴታን በመወጣት መብትዎትን ይጠይቁ።

**ማጣቀሻ**

3. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብልክ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1995

4. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 209/2002
5. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የምኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995
6. የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 1157/2011
7. የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 609/2001
8. የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008
9. በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ስለተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/1996 እና 21/1997
10. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሲሰረዝ በእጅ ያለን ዕቃ ዋጋ ስለማስላትና ታክስ ስለሚቀናነስበት መመሪያ ቁጥር 24/2001
11. በኢትዮጲያ ገቢዎች ሚኒስቴር የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 148/2011
12. በገሸሁ ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2012